**ሠላም ይስንፈን - ፆታዊ ጥቃት ይቁም!**

የ16 ቀናት በፆታዊ ጥቃት እንቅስቃሴ ላለፉት 25 አመታት በሃገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሴቶችን ጥቃት ለማስቀረት በሚደረገው እንቅስቃሴ የማስተባበር ተግባር መታሰቢያነት ሲውል ቆይቷል፡፡ ኖቬምበር 25 ዓለም አቀፍ የሴቶች ጥቃት መከላከል ቀን እና ዲሴምበር 10 የሰብአዊ መብት ቀን የተመረጡት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማስቀረት እና የሰብአዊ መብት ዕሴቶች ቁርኝትን አፅንኦት ለመስጠት እና የሴቶች ጥቃት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጥሰት መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ ዘንድሮም ይህ ዓለም አቀፍ ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት እንቅስቃሴ ከህዳር 16 እስከ ታህሳስ 1 ቀን 2014 በተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል፡፡ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን የመቃወም የ16 ቀናት ንቅናቄ - የኢትዮጲያ ቡድን በሀገራችን ተንሰራፍቶ የሚገኘውን የፆታዊ ጥቃት ተግባር ለመታገል ብሎም ለማስቀረት በማሰብ ቁጥራቸው 14 የሆኑ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪል ማህበራት ያቋቋሙት የጋራ የዘመቻ ቡድን ሲሆን የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (ኢ.ሴ.ማ.ቅ) የዘመቻ ቡድኑን በማስተባበር የተለያዩ ስራዎችን አየሰራ ይገኛል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ እነዚህን ቀናት በኅብረት ለማሰብና ብሎም በሴቶች ላይ ከፍተኛ ችግር እያደረሰ ያለውን የፆታዊ ጥቃት ተግባር አገራዊ አጀንዳ አድርጎ ለመስራት በ1998 ዓ.ም. የተቋቋመው ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የመቃወም የዘመቻ ቡድን ወይም /Gender Based Violence Campaign Ethiopia – GBVC-E/ ቀናቱን በጋራ በማሰብ እና የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ሲያከብር ቆይቷል፡፡

ይህም ብሔራዊ የዘመቻ ቡድን ጾታን መሠረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ በርካታ ስራዎችን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል ከመንግስት ሰራተኞች፣ ከፖሊስ፣ ከመገናኛ ብዙሃን፣ ከወጣቶች፣ ከተማሪዎች፣ ከፋብሪካ ሰራተኞች፣ ከአበባ ፋርም ሰራተኞች፣ ከስደተኞች ጋር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ከማከናወን አልፎ ፆታዊ ጥቃትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ የተለያዩ የግፊትና የትብብር ስራዎችን አከናውኗል፡፡

የ16 የንቅናቄ ቀናት እንደሁልጊዜውም ፆታን መሰረት ባደረገ ጥቃት ላይ የሚደረገውን ዘመቻ እየተደጋገሙ ያሉ በሴቶች ላይ የሚደርሱ የጥቃት ወንጀሎችን በተለይም በግጭት እና ከመኖሪያ አካባቢ በመፈናቀል ምክንያት በሚደርሱ ፆታዊ ጥቃቶች ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ይከበራል፡፡ ፆታዊ ጥቃትን በመቃወም ላይ ትኩረት ያደረጉት እነዚህ የእንቅስቃሴ ቀናት በዚህ ዙሪያ የሚሰሩ አካላት በማሰባሰብ እና ልምዶችን በመለዋወጥ የተገኙ ውጤቶችንና ያጋጠሙ ችግሮችን ወደ ኋላ መለስ ብለው የሚመለከቱበት፤ ከዚያም አልፎ ውሳኔ ሰጪው መንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ለጉዳዩ የበለጠ ትኩረት እንዲሰጡ የሚጠይቁበትና ድምፃቸውን የበለጠ እንዲሰማ የሚሰሩበት ወቅት ነው፡፡

የዘንድሮው አለም አቀፍ የ16 ቀናት ንቅናቄ መሪ ሃሳብ "ብርቱካናማ አለም፡ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች አሁን ይቁሙ!" የሚል ነው። የዘመቻ በፆታዊ ጥቃት - ኢትዮጲያ ቡድን ይህን መልእክት እየደገፈ፤ ሀገራችን በአሁኑ ወቅት የምትገኝበትን ሁኔታ እና በጦርነት፣በግጭቶች እና በመፈናቀል ምክንያት ሴቶችና ህጻናት እየደረሰባቸው ያለውን ከፍተኛ ችግር እና ስቃይ ለማጉላት የሚያስችል መሪ ቃል አዘጋጅቷል። በመሆኑም ወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታን ታሳቢ በማድረግ "ሠላም ይስንፈን - ፆታዊ ጥቃት ይቁም!" በሚል የመልዕክት ርዕስ ከባለ ድርሻ አካላቱ ጋር በቅንጅት ያከብራል። የዘመቻ ቡድኑ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን የተለየየ ፆታዊ ጥቃት እና ስቃይ ለመግታት የሰላም ዕውን መሆን የመጨረሻ መፍትሄ እንደሆነ ያምናል።

መሪ ቃሉ የተመረጠው በሀገራችን በተለያየ ጊዜ እና ቦታ እየተከሰተ ያለው ግጭት እና ጦርነት ተከትሎ ሴቶችና ወጣት ሴቶች በአመዛኙ የችግሩ ገፈት ቀማሽ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ጦርነቱ የወለዷቸው መጠነ ሰፊ ችግሮች በኢትዮጵያ ዜጎች፣ ንጹሃን ነዋሪዎች፣ ከመኖሪያ ቀያቸው በተፈናቀሉ ሴቶች እና ህፃናት ብሎም ከሌሎች ሀገራት በስደት መጥተው በተጠለሉ በርካታ ሴቶችና ህጻናት ላይ የስቃይ መነሾ ሆነዋል። ዜጎች ከመኖሪያ ቀዬአቸው በብዛት ሲፈናቀሉ በእድሜ ሊጋ የሆኑ ሴት ህፃናት ሳይቀሩ ለአስገድዶ መደፈር እና ሌሎች ጾታዊ

ጥቃቶች እንዲዳረጉ ሆኗል፡፡ በጦርነቱ አስገድዶ መድፈር እንደ ጦር ስልት በመታየቱ በርካታ ሴቶች የዚህ አስከፊ ድርጊት ሰለባ ሆነዋል። በዚህም ምክንያት የሴቶችን ጤንነትም ሆነ ሰብዓዊ ክብር ለመጠበቅ አዳጋች ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ የዚህ ዓመት ፆታን መሰረት አድርጎ የሚፈጸምን ጥቃት ዘመቻ፤ መሪ ቃሉን በማጉላትና የቅስቀሳ ስራዎች በመስራት በሴቶች ላይ የሚፈፀመው ፆታዊ፣ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ጥቃትን ለማስቀረት አላማ አስቀምጦ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ይተገበራል፡፡ እንቅስቃሴዎቹ የሚደረጉት በዘመቻ ቡድኑ አባል ድርጅቶች እና የሲቪል ማህበራት ሲሆን በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች በ16ቱ ቀናት ውስጥ የሚከበሩ ዓለም አቀፍ ቀናት ላይ ትኩረት በማድረግ ይሆናል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በዋናነት፡-

ህዳር ***16*** **-** ዓለም ዓቀፍ የነጭ ሪቫን ቀን

ህዳር ***20*** **-** ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ተከላካዮች ቀን

ህዳር ***22*** **-** ዓለም አቀፍ የኤድስ ቀን

ህዳር ***25*** **-** ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀን

ህዳር ***27*** **-** ዓለም አቀፍ የጥቃት ሰለባዎች ቀን

ህዳር ***30*** **-** ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ቀን ናቸው።

በዚህም አጋጣሚ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የመቃወም የዘመቻ ቡድን (GBVC-G) "ሠላም ይስንፈን **-** ፆታዊ ጥቃት ይቁም!" እያለ ለኢትዮጵያ ሠላም፤ ብሎም ለጾታዊ ጥቃት መቆም ማህበረሰቡ በሙሉ የበኩሉን እንዲያደርግ እና ሃላፊነቱን እንዲወጣ እያሳሰበ በተለያዩ ግጭቶች እና ጦርነት ውስጥ ያሉ ወገኖች ሰላማዊ መፍትሄዎችን እንደአማራጭ የመውሰዱን ሂደት አጠናክረው እንዲቀጥሉ፤ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ፆታዊ ጥቃትን አስመልቶ ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ የትም! በማንም ፆታዊ ጥቃት እንዳይፈፀም በመከላከል የበሉሉን ሃላፊነት እንዲወጣ እንዲሁም በግጭቶች እና ጦርነት ምክንያት ለተፈናቀሉ ወገኖች የበኩሉን ድጋፍ እንዲያደርግ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡